የሰ/መ/ቁ.78865
ጥር 28 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት

ተጠሪዎች ፡- 1. አቶ ገ/ስላሴ ኃ/ማርያም
2. ወ/ት እቴቱ ለማ
3. ወ/ት አማረች መንግስቴ
4. ወ/ሮ ለምለም እንዳለ
5. አቶ አካለወርቅ ሳልልህ
6. አቶ አርአያ ውብነህ
7. ወ/ሮ በቀለች ከበደ
8. አቶ እስማኤል ዓሊ

(ከ1–8 ያሉት፦) ጠበቃ ዘነበ ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሆኖ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ድርጅት ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- ተከሳሽ ድርጅት ባካሄደው የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ መሰረት በተጠናው የደመወዝ እስኬል ለእያንዳንዱ የሥራ መደብ መነሻ ደመወዝ ሲወሰን ከሳሾች በተመደብንበት የሥራ መደብ ማግኘት የሚገባንን ሲወስን ቀደም ሲል ስናገኝ የነበረውን ደመወዛችንን የቀነሰብን ስለሆነ ያለአግባብ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክልልን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ለክሱ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ፤-በተከሳሽ ድርጅት መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተደርጎ በመንግስት ከጸደቀ በኋላ በአማካሪ ድርጅት የተጠናውን አዲስ የደመወዝ እስኬል መነሻ በማድረግ ከሳሾች ክሱን ያቀረቡ ስለሆነና የደመወዝ ጭማሪን የሚመለከት ክስ የወል የሥራ ክርክር ስለሚሆን መቅረብ ያለበት ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በቀጥታ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ደ/መቃወሚያ ላይ በሠጠው ብይን፡- ከሳሾች ባቀረቡት ክስ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ጠቅላላ የደመወዝ እስኬል አሰራርን የሚነካ በመሆኑና ውጤቱም በሌሎች ሠራተኞች ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ስለሚችል በወል የሥራ ክርክር የሚሸፈን በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ክሱን ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በሚል የክሱን መዝገብ ዘግቷል፡፡

የስር ከሳሾችም የመ/ደ/ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ቅር በመሠኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሠጠው ፍርድ ይግባኝ ባዮች ባቀረቡት ክስ ላይ የሚወሰነው ጭብጥ ተቋረጠብን የሚሉት የደመወዝ ጭማሪ ነው? ወይስ ድጎማ ነው? የሚለው ሲሆን በዚሁ ጭብጥ ላይ የሚሰጠው ውሳኔም ከይግባኝ ባዮች አልፎ የሁሉንም ሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚነካ ባለመሆኑ ጉዳዩ በግል የሥራ ክርክር የሚታይ ነው በማለት የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በመሻር በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ክርክሩን መልሶለታል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 147(2) መሰረት በወል ሥራ ክርክር የሚሸፈን ሆኖ እያለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በግል የሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው በማለት ጉዳዩን የሥራ ክርክር ችሎት እንዲወስነው የመለሰው ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎቸ በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- ክሱ የቀረበው አመልካች ድርጅት ሲከፈለን በነበረው ደመወዝ ላይ መዋቅሩን መሥራት ሲገባው ደመወዛችንን በመቀነስ መዋቅሩን የሰራ በመሆኑ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክል ዳኝነት የጠየቅንበት እንጂ ክርክራችን በተሰራው መዋቅር ላይ ባለመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ክሱ በግል ሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ነው ሲል የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለው ሊጸና ይገባል በሚል ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ድርጅትም ለተጠሪዎች መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በወል የሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው? ወይስ በግል ሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የግል የስራ ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የሚታዩ ስለመሆናቸው ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138 መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የወል ሥራ ክርክር ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሚታይ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 142(1)፣147(1)(ሀ) ተመልክቷል፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ምላሽ የሚሻው ጉዳይ ግን አንድ ጉዳይ የግል ወይም የወል የሥራ ክርክር ሊባል የሚችልበት አግባብ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/18180 በቀን 29/11/1997 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በዚሁ የህግ ትርጉም መሠረትም አንድ ጉዳይ የወል የሚያሰኘው የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ሲሆን ክርክሩ የግል ነው የሚባለው ደግሞ ዉጤቱ በተከራካሪ ሠራተኛ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሲሆን ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ቀደም ሲል ሲናገኙ የነበረውን ደመወዝ አመልካች

ያለአግባብ በመቀነስ በተሰራው መዋቅር ላይ ያስቀመጠው ስለሆነ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክል ይወሰንልን በሚል ክስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም ቀደም ሲል በድጎማ መልክ ከደመወዛቸው ጋር ሲከፈላቸው የነበረው ገንዘብ ከደመወዛቸው ተቀንሶ በተሰራው መዋቅር ላይ ከመቀመጡ በስተቀር በደመወዛቸው እስኬል መሰረት ማግኘት የሚገባቸው ገንዘብ አልተቀነሰም በሚል ተከራክሯል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቀደም ሲል መዋቅሩ ከመሰራቱ በፊት ሲከፈላቸው የነበረው የደመወዝ መጠን የድጎማ ክፍያ ተጨምሮ ነው? ወይስ ሳይጨመር ነው? ድጎማው ተቀናሽ ተደርጎ በተሠራው መዋቅር መሰረት የደመወዝ እስኬል ሲቀመጥ ተጠሪዎቹ ማግኘት ከሚገባቸው የደመወዝ መጠን ቀንሷል? ወይስ አልቀነሰም? የሚሉ ነጥቦች ከተጣሩ በኋላ የሚሰጠው ውሳኔ ደግሞ ከተጠሪዎች አልፎ የሌሎች የድርጅቱን ሠራተኞች መብትና ጥቅም በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ሊነካ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች መዋቅሩ ሲሠራ ቀደም ሲል ስናገኝ የነበረው የደመወዛችን እስኬል ተቀንሶብናል በማለታቸው ብቻ ጉዳዩ የወል ሥራ ክርክር ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት ባለመኖሩ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዎቹ ያቀረቡት ክስ በግል የሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ነው ሲል በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/115821 በቀን 10/7/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በግል የስራ ክርክር የሚሸፈን በመሆኑ ሊቀርብ የሚገባው ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ነው በሚል ከፍተኛው ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ